# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# አረንጓዴ ዐሻራ - ለግድቦች ደኅንነትና ውጤታማነት

ኢያሱ መሰለ

ኢትዮጵያ የአፍሪካ የውሃ ማማ እየተባለች እንድትጠራ ያስቻላት በገጸ-ምድር እና በከርሰ-ምድር የውሃ ሃብት የበለጸገች በመሆኗ ነው:: የውሃ ሃብቷ ተጠብቆ እንዲኖር ከሚያስችሉ ጉዳዮች አንዱ የደን ሃብቷ መጠበቅ ነው:: የደኖች መኖር አርጥበት አዘል አየር እንዲፈጠር በማድረግ የዝናብ እጥረት እንዳይኖር ያደርጋል:: ዝናብ ሲኖር ወንዞችና ሐይቆች ይሞላሉ፣ የከርሰምድር የውሃ ሀብት ክምችትም ይጨምራል:: ውሃ የተፈጥሮን ሚዛን ከማስጠበቅም ባሻገር ወደ ተለያዩ ኢኮኖሚዎች መመንዘር የሚችል ትልቅ ሀብት ነው:: ይህንን ሀብት አስጠብቆ ለመኖር የደን ሽፋንን ማሳደግ አስፈላጊ ነው:: ደን ያለ ውሃ ውሃም ያለደን ሕልውናቸውን ማረጋገጥ ስለማይችሉ ሁለቱም ተመጋግበው የሚኖሩበትን የተፈጥሮ ሕግ ለማስቀጠል እየተመናመነ የመጣውን የደን ሀብት ማከም ግድ የሚል ነው::



ኢንጂነር አሸብር በኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር



በሞጆ ሃዋሳ ፍጥነት መንገድ የተቋሙ ሠራተኞች የአረንጓዴ ዐሻራ ተሳትፎ

ዓለም አሳሳቢ ለሆነው የደን መመናመን እየሰጠ ያለውን ትኩረት ተከትሎ በኢትዮጵያም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር ተግባራዊ ተደርጎ ባለፉት አምስት ዓመታት ብቻ ከ32 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል:: በዘንድሮው የክረምት ወቅትም “የምትተክል ሀገር፣ የሚያጸና ትውልድ” በሚል መሪ ሀሳብ ከ7 ነጥብ 6 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን ለመተከል ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል:: በዚህ ችግኞችን የመትከል ንቅናቄ የሀገሪቱ ዜጎች በተለያዩ መልኮች እየተሳተፉ ይገኛሉ፤ የመንግሥት ተቋማትም ግንባር ቀደም ተዋናይ በመሆን ለሌሎች አርዓያ ያሚደርጓቸውን ተግባራት በማከናወን ላይ ናቸው::

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አመራሮችና ሠራተኞችም በየዓመቱ እንደሚያደርጉት ሁሉ በዘንድሮው ዓመትም በተለያዩ ቦታዎች አረንጓዴ ዐሻራቸውን እያኖሩ ይገኛሉ:: የዛሬው ጽfከፋችንም የተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች ከሰሞኑ በኮይሻ የውሃ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት እና በሞጆ ሃዋሳ የፍጥነት መንገድ ላይ ተገኝተው ስላከናወኑት የችግኝ ተከላ መርሐ-ግብር የሚያስቃኛችሁ ይሆናል::

በኮይሻ የውሃ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ችግኞችን መትከል እና አካባቢን መጠበቅ በፕሮጀክቱ እቅድም ውስጥ ያለ ተግባር በመሆኑ ቀደም ሲልም ግድቡን ከደለል ለመከላከልና የሥራ ቦታውን ነፋሻና ምቹ ለማድረግ በርካታ ችግኞች ተተክለዋል:: የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር ከተጀመረ በኋላም በየዓመቱ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም ይደረጋል::

ባለፈው ሳምንትም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋና ሥራ አስፈፃሚው ኢንጂነር አሸብር ባልቻ እና ሌሎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት በኮይሻ የውሃ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር ተካሂዷል:: በዚሁ ወቅት ኢንጂነር አሸብር እንደተናገሩት የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ ግድቦች በደለል እንዳይሞሉና ተጨማሪ ውሃ እንዲይዙ እያገዘ ይገኛል። የተቋሙ ሠራተኞች በምግብ ራሳቸውን እንዲችሉ ተቋሙ ለምግብነት የሚውሉ ችግኞችን እየተከለ እንደሆነም ገልፀዋል። ሠራተኛው በአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ ላይ በስፋት መሳተፍ እንደሚኖርበት አሳስበዋል።

የኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አቶ መብራቱ ተሾመ በበኩላቸው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሩ የአካባቢውን ሥነ ምሕዳር በመጠበቅ የሥራ ቦታዎችን ለኑሮ ምቹ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

በፕሮጀክቱ የአካባቢያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ቢሮ ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛቸው ደሳለኝ እና በዩ ቢዩልድ ኩባንያ የኢንቫይሮሜንታል መሐንዲስና የችግኝ ተከላ ፕሮግራሙ አስተባባሪ ሄኖክ ቸኮል እንደተናገሩት በፕሮጀክቱ የግንባታ ሥራ ምክንያት የተጎዱ ቦታዎችን ወደ ነበሩበት ለመመለስ ሲባል የችግኝ ተከላ ሥራው በሀገር አቀፍ ደረጃ የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ ከመጀመሩ በፊት ይከናወን ነበር። በአሁኑ ወቅት የፕሮጀክቱ ሠራተኛ የችግኝ ተከላ ሥራውን እንደ ዋና ሥራ በመያዝ መኖሪያ ቦታውን ምቹ እያደረገ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ በየዓመቱ የተተከሉት ችግኞች አሁን ላይ ፍሬ ማፍራት መጀመራቸውን እና ሠራተኛውም ለምግብነት እየተጠቀማቸው መሆኑን ገልጸዋል::

መርሐ ግብሩ ላይ የአዳማ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ መንግሥቱ ባልቻ እና በገቢዎች ሚኒስቴር የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛው በኩረፂዮን ተገኝተዋል::

ከዚህም ሌላ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አመራሮችና ሠራተኞች የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ባዘጋጀው ሞጆ ሐዋሳ የፍጥነት መንገድ ላይ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አከናውነው ነበር።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሙላት ገዛኸኝ እንደገለጹት ተቋሙ ከተጣለበት ሀገራዊ ኃላፊነት ባሻገር ባለፉት ዓመታት በተከናውኑ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሮች ላይ በንቃት ሲሳተፍ መቆየቱን ተናግረዋል:: ተቋሙ በሁሉም የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች የተጠናከረ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም እያካሄደ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የአካባቢ ጥበቃን ለማጎልበት ከአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ የተቀዳ የታዳሽ ኃይል አማራጮችን በመጠቀም የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት እና በማስተላለፍ አረንጓዴ እና ፅዱ ኢትዮጵያን ለመፍጠር ተቋሙ በቁርጠኝነት እየሠራ ይገኛል ብለዋል::

በችግኝ ተከላ መርሐ-ግብሩ ላይ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ኃይለሚካኤል፣ የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ኃላፊ አቶ ሙሱጠፋ አባሲመል፣ የሞጆ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባን ጨምሮ አስራ ሁለት የመንግሥት የልማት ድርጅት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ተሳትፈዋል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ